# የኢትዮጵያ ርሀብና ችጋር መንስኤው ምንድን ነው?

አቻምየለህ ታምሩ

ኢትዮጵያ ውስጥ የተከሰተውን ርሀብና ችጋር በሚመለከት ሰፊ ትንተና የያዘ ረዘም ያለ ጽሁፍ ለማዘጋጀት ሳስብ ነበር። ለጽሑፌም የሚሆኑ ማስረጃና ማጣቀሻ ወረቀቶችን ከያሉበት አሰባስቤ ነበር። ሆኖም ግን ብዙ ሰው ረጅም ጽሁፍ ከማንበብ ይልቅ በፌስቡክ የሚለቀቁ «አርቲቡርቲ» ቪዲዮች ላይ በማተኮሩ ረጅም ጽሁፍ በአማርኛ መጻፉ አጉል ድካም መሆኑን በመገንዘቤ ድካም የሌለበትን መተውን መርጫለሁ። የአገራችንን ርሀብና ችጋር መንስኤ በሚመለከት ግን በአጭሩ የሚከተለውን ማቅረብ እፈልጋለሁ።

ርሀብ ማለት «አንድ ሰው በቀን የሚያስፈልገውን በቂና ተመጣጣኝ ምግቦች ባለማግኘት የአካልና የአእምሮ እድገት አጥቶ በመጫጫት ሲኖር ነው»። ችጋር ማለት ደግሞ «የሚላስ፣ የሚቀመስ በመጥፋቱ ሰዎች በአካላቸው ውስጥ በአከማቹት እየተጠቀሙ፣ ዕለት በዕለት አካላቸውን እየጨረሱ፣ እያወቁት ቀስ በቀስ ወደተረጋገጠ ሞት የሚሄዱበት የኅብረተሰብ በሽታ ነው»። ለነገሩ የህይዎታችን መልኮች ስለሆኑት ርሀብና ችጋር ለኛ ለኢትዮጵያውያን መናገር ለቀባሪው ማርዳት ነው የሚሆነው።

ርሀብና ችጋር የተፈጥሮ አደጋዎች አይደሉም። ከተፈጥሮ ጋርም ቀጥተኛ ግንኙነት የላቸውም። ስለዚህ ርሀብም ሆነ ችጋር የከፋ ድህነት መገለጫዎች እንጂ የድርቅ ውጤቶች ሊሆኑ አይችሉም።

«ግብርና መር» በሆነችዋ አገራችን ዛሬ እየተለመነ ያለው ለሸማቹ ማህበረሰብ ሳይሆን ለገበሬው ወይንም ላምራቹ ነው። ለአስር ተከታታይ አመታት በግብርና መር ኢኮኖሚ «በሁለት አሃዝ አደገች» በተባለችዋ አገራችን ዛሬ ጊዜያዊ ርሀብና ችጋር እየመተራት ያለው ግብርና እየመራ «በሁለት አሀዝ» «ባደገችባቸው» ያለፉት አስር ተከታታይ አመታትና ጥሩ በተባለው ጊዜ ውስጥ ትርፍ ማምረት ስላልቻለች ወይንም ስለማትችል ነው። ግብርና እየመራ «በሁለት አሀዝ» ባደግንባቸው ያለፉት አስር ተከታታይ አመታትና ጥሩ በተባለው ጊዜ ውስጥ ትርፍ ማምረት የቻልን ቢሆን ኖሮ ዛሬ ጊዜያዊ ርሀብና ችጋር ሲቆላን ወይ እህል አለዚያም ደግሞ በቂ መሸመቻ ገንዘብ ይኖረን ነበር። ግብርና እየመራ «በሁለት አሀዝ» ባደግንባቸው ያለፉት አስር ተከታታይ አመታትና ጥሩ በተባለው ጊዜ ውስጥ ግብርና ያደገ ቢሆን ኖሮ ዛሬ ጊዜያዊ ርሀብና ችጋር ሲከሰት ቀዳሚው የአደጋ መከላከያ ዘዴያችን ምጽዋትና ርዳታ አይሆንም ነበር። ስለዚህ ኢትዮጵያ ዛሬ እየተራበች ያለችው በዚህ አመት ኤልኒኖ ስለተከሰተ ሳይሆን ጥሩ በተባሉት ያለፉት አስርና በላይ አመታት ጊዜ ውስጥ ትርፍ ማምረት ባለመቻሏ ብቻ ነው።

ከዚህ ተነስተን መጠየቅ ያለብን ትልቁ ጥያቄ ለምንድን ነው ጥሩ በሚባል ወቅት ወይንም ዝናብ በበቂ ሁኔታ በዘነበባቸው ያለፉት አስርት እመታው ጊዜ ውስጥ ትርፍ ማምረት ያልቻልነው? የሚል ይሆናል። በኔ አስተያየት ጥሩ በሚባል ጊዜ ኢትዮጵያ ትርፍ ማምረት ያልቻለችው ጥሩ የመንግስት ፖሊሲ ስለሌላት ወይንም በፖሊሲ ችግር ምክንያት ብቻ ነው። ዛሬ በአገራችን የተከሰተው ርሀብና ችጋር ለጊዜያዊ ርሀብና ችጋር ዘለቂ መፍትሔ መስጠት የማይችል የኢኮኖሚ ፖሊሲ ውጤት ነው። 85% በትናንሽና አነስተኛ ማሳ ላይ የተሰማራ ገበሬ ማለት 85% ለጊዜያዊ ርሀብና ችጋር የተጋለጠ የህብረተሰብ ክፍል ማለት ነው። ይህ ማለት ግን አሁን የተከሰተው የኢትዮጵያ ጊዜያዊ ርሀብና ችጋር 85% የሚሆነው አነስተኛ ገበሬ ድሀ ስለሆነ ወይንም ኢትዮጵያ ሀብት ስለሌላት የተከሰተ ነው ማለት አይደለም። ችግሩ የተከሰተው ኢትዮጵያ በመንግስትነት በተሰየሙ ነውረኞች እጅ ወድቃ ሀብትና ንብረቷ በእፍረተ ቢስ ወሮበሎች ተዘርፎ ብዙ ቅን ኃሳቦች እንዲመክኑ ተደርገው የኢኮኖሚ ቀውስ ውስጥ በመግባቷ ነው። ስለዚህ ኢትዮጵያ ውስጥ አሁን የተከሰተው ርሀብና ችጋር ብቻ ሳይሆን የኢኮኖሚ ቀውስም ጭምር ነው። የርሀብና ችጋሩ እንዲሁም የኢኮኖሚ ቀውሱ ምክንያት ደግሞ ከአጠቃላይ የወያኔ ስርዓት የኢኮኖሚ ፖሊሲ ችግር ባሻገር የስራ ተነሳሽነትን የሚገፋፉና የሚረዱ ፖሊሲዎች አለመኖራቸው፤ ተቋሞችና አሰራሮች አለመስፈናቸው፤ እንዲሁም አገዛዙ በግለሰቦች ነጻነት ላይ ያለው ተጽዕኖ ገደብ የለሽ መሆኑ ነው።

የሰብዓዊ ፍጡር አዕምሮ ከእስር ሲለቀቅና ነጻ ሆኖ ማሰብ ሲጀምር የመፍጠር አቅሙ ተሟልቶ ይከሰትና የማይናቅ የፈጠራ ቅርስ ያኖራል፤ የስልጣኔ ማዕበልም ያስነሳል። የማይከጅሉ ንጹህ እጆች የነበሩት

ያያቶቻችን ትውልድ ዛሬ የምንኮራባቸውን ቅርሶች አኑሯል። በዘመኑ የነበሩ ትውልዶች አእምሯቸው ውስጥ በጠነሰሷቸው መልካም አስተሳሰቦችና ብሩህ ርዕዮች ገንቢ ሐሳብ ለማመንጨትና በጋራ ተግባራዊ ለማድረግ በመቻላቸው ዛሬ የምንኮራበት ቀደምት ስልጣኔ ሊከሰት ችሏል። ዛሬ ግን እድሜ ለወያኔ የሚያኮሩንን ነገሮች ሁሉ አዋርዶ፤ ልናፍርባቸው በሚገቡ ወራዳ ተግባሮች እየኮራን ነጻነት ሽብርተኛነት ሆኖ በህሊያ ማሰብ የሚጠይቁ ሙያዎች ሁሉ በአሽባሪነት የሚያስቀስፉ አደገኛ መከራዎች በመሆናቸው በነጻነት ማሰብ ከህጻናት የአእምሮ ሰሌዳ ላይ እየተፋቀ ነው።

ከፍ ብሎ የቀረበው ሀተታ ሲጨመቅ የአገር የኢኮኖሚ እድገት ግለሰቦች ህይወታቸውን ለማሻሻል የሚያደርጉት ጥረት ጥምር ውጤት መሆኑን ማየት እንችላለን። በግልጽ እንደሚታየው እብሪትና ድንቁርና «ያጀገነው» ወያኔ ግን አይደለም በኢትዮጵያውያን መካከል ለእድገት መሰረት የሆነውን የውስጥ ነጻነት ስሜት እንዲፋፋ ሊያደርግ የመንግስትን የአስተዳደርና የስለላ መዋቅር ሁሉ በሰፊው ዘርግቶ በግለሰብና በቤተሰብ ደረጃ የሚወሰኑ የእለት ተእለት የኑሮ ውሳኔዎችን እንኳ ሳይቀር በመንግስት መልካም ፈቃድ የሚከወኑ አድርጓቸዋል። አሁን አሁን ደግሞ የእለት ተእለት ኑሯችን ብቻ ሳይሆን ህይወታችንም በመንግስት ይሁንታ ስር እንዲወድቅ አድርጎታል።

አማርተያ ሰን «የአምባገነን መንግስታት ችግር» ብሎ እንዳስቀመጠው የወያኔ የኢኮኖሚ ፖሊሲም ችግሩ ርሀብና ችጋር እንዳይከሰቱ የሚያደርጉ ህዝባዊ ተቋማትን አለመፍጠሩ ብቻ ሳይሆን ርሀብና ችጋር ከተከሰተ በኋላም ቢሆን እልቂትን ለመታደግ የሚያስችል ርዳታ እንኳ ቢገኝ ወያኔ የገነባቸው «ተቋማት» ስልጣንን ተጥቅሞ አገርን ለመግፈፍ የተዘረጉ የዘረፋ መዋቅሮች ስለሆኑና በሙስናና በስርቆት ማነቆዎች ስለተተበተቡ በወያኔ ተቋማት የርሀብና ችጋርን ጉዳት መቋቋም አይቻልም። ለዚህ አስረጅ የሚፈልግ ቢኖር ወያኔ የምዕራባውያን እርዳታ እንዴት በ1977 ዓ.ም. ለማለሊት ድግስና ለጥይት መገዣ እንዳዋለውና በ1997 ዓ.ም. የተከሰተውን ድርቅ ተከትሎ የተሰጠውን የርታዳ ገንዝብም የተወሰነ ፍርፋሪ ብቻ ለደጋፊወቹ በትኖ የተቀረውን በመዝረፉ በርሀብና ችጋር የረገፈው ቁጥር የትየለሌ መሆኑን ማስታወሱ ብቻ ይበቃል።

Thirukodikaval Nilakanta Srinivasan የተባለ የየል ዩኒቨርሲቲ የኢኮኖሚክስ ፕሮፌሰር መንግስት እንደ መንግስት ርሀብና ችጋርን ሊቀርፍ የሚችለው የፖለቲካ ነጻነት እንዲሰምር የኢኮኖሚ ነጻነት ሲያውጅ ነው ይላል። ይህ የኢኮኖሚስቱ ምክረ ሀሳብ የሰዎች ነጻነት መስፋት የኢኮኖሚ እድገት መሳሪያም ግብም ነው ከሚለው እውቀት ጋር መሳ ለመሳ ይሄዳል፤ የሰዎች ነጻነት ሲባል የኢኮኖሚ ነጻነትትንም ይጨምራልና። የኢኮኖሚ ነጻነት ሲባል ደግሞ ዋነኛው የመሬት ባለቤትነት ወይንም የመሬት ይዞታ መብት ነው። ስለዚህ የኢኮኖሚ ነጻነት ሳይኖር ርሀብና ችጋርን ማጥፋት አይቻልም ማለት ነው። ከዚህ ተነስተን በማይለቅ የመሬት ቁጥጥር ፍቅር የፈደቀው የወያኔው የመሬት ፖሊሲ ርሀብና ችጋርን የሚያጠፋ መድሀኒት ሳይሆን ርሀብና ችጋርን የሚፈጥር ቫይረስ መሆኑን መገንዘብ እንችላለን።

የSussex Universityው የልማት ምጣኔ ሀብት ምሁሩ ፕሮፌሰር Stephen Devereux ደግሞ laissez-faire economic policy ያላቸው አገሮች የመንግስታቱ መጠን [the size of government] ትንሽ ስለሆነ የምግብ ዋስትናን ለማስጠበቅ የሚኖራቸው ሚናም በዚያው መጠን የተወሰነ ነው ይለናል። በነዚህ አገሮች ለሚከሰት የምግብ ዋስትና ጉድለትም የመንግስታት ፖሊሲ ተጽዕኖ አናሳ እንደሆነ ይነግረናል። እንደኛ አይነት laissez-faire economic policy በሌላቸው አገሮች ግን የመንግስት የኢኮኖሚ ድርሻ የፈረጠመ በመሆኑና የመንግስቱም መጠን [ the size of government] ትልቅ ስለሆነ የሚከሰተው የምግብ ዋስትና ችግር ከመንግስት ፖሲሊ ጋር ቀጥተኛ ቁርኝት አለው። ስለዚህ የወያኔ መንግስት laissez-faire የሚባል አይነት መንግስት ስላልሆነ በፕሮፌሰር Stephen Devereux ጥናት መሰረት የኢትዮጵያ ርሀብና ችጋር አዙሪት ከአገዛዙ የኢኮኖሚ ፖሲሊ ድክመት የሚመነጭ መሆኑን በርግጠኝነት መናገር ይቻላል ማለት ነው።

ባጠቃላይ በደንቆሮዎች ፖሊሲ የተነሳ አለም ያወቀው የርሀብና ችጋር መፍትሔ እያለ ያገራችን ትንሹ ችግር ትልቅ መስዕዋትነትን እያስከፈለን ይገኛል። በደንቆሮዎች ፖሊሲ የተነሳ ኢትዮጵያ ከሀምሳ አመታት በፊት በአገር ውስጥ ታመርታቸው የነበሩትን ምርቶች ዛሬ ከውጭ አገር የምታስገባቸው ውድ ሸቀጦች ሆነዋል። በደንቆሮዎች ፖሊሲ የተነሳ ርሀብና ችጋርን ማሸነፍ የሚቻለው ቢሊዮን ዶላር በሚከፍሏቸው የፈረንጅ የህዝብ ግንኙነት ተቋማት [ PR firms] አማካኝነት አለማቀፍ የዜና ማሰራጫዎች በደርግ ዘመን «famine is

looming» በማለት እንደወረደ ያቀርቡት የነበረውን የኢትዮጵያ ርሀብና ችጋር ገመና በወያኔ ዘመን ግን ተለሳልሶ «drought is looming» በሚል እየቀረበና የወያኔ ገመና በህዝብ ግንኙነት ስራ እየተደበቀ፤ ምጽዋቱ ግን ፌለፌትና በጀርባ ከጥራጥሬ ጀምሮ እስከ ቢሊዬኖች ዶላር እርዳታ እየተንጋጋና ለርሀብተኛውና ለተቸገረው የማይደርስ የልመና መዝገብ ቋሚ ደንበኞች ሆነን ችግሩ በኖራ ቅብ [white wash] ተሸፍኖ በማለፍ ሆኗል። በደንቆሮዎች ፖሊሲ ትላልቅ ፕሮጀክቶች የሚታቀዱት በትልቁ ለመዝረፍ እንጂ ለትልቅ ራይዕ አይደለም። በደንቆሮዎች ፖሊሲ ተርበን እንደጠገብን ይነግሩናል። በደንቆሮዎች ፖሊሲ በዜግነታችን የምናገኛቸው መብቶቻችችን ተነጥቀን በታማኝነታችን የምናገኛቸው የወያኔ የግል ንብረቶች ሆነዋል።

…

ስለዚህ አለም ያወቀው የርሀብና ችጋር መፍትሔ እያለ ከርሀብና ችጋር ዝንታለም እየኖርን ያለነው በድንቁርና የተሰራውን የዱርዬ ስርዓት ወደ እውቀት ስርዓት ለማሸጋገር መፍትሄ ፍለጋ ላይ ብዙ ጊዜ በመባዘናችን ነው ማለት ይቻላል።

አበቃሁ!

[ኢትዮሚድያ - Ethiomedia.com](https://www.ethiomedia.com)

May 2, 2016